TELETHON KIDS INSTITUTE
Discover. Prevent. Cure.

map


## ማጠቃለያ

### መነሻ

እ.ኤ.አ. ከ 2000 ጀምሮ በአፍሪካ ውስጥ ያለውን የወባ በሽታ ከመቀነስ አንጻር ጉልህ መሻሻል ታይቷል ፤ ነገር ግን የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወሳኝ የሆኑ የወባ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ መንገዶችን የሚያስተጓጉል ከሆነ ከዚህ በፊት የታዩ መሻሻሎች ለአደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ። የዚህ ጥናት ዓላማ የወባ መቆጣጠሪያዎች በተለያየ ደረጃ መቋረጥ በወባ በሽታ መከሰት እና ሞት ላይ ሊያስከትለው የሚችለውን አሳማኝ ውጤት መገምገም ነበር::

### ዘዴዎች

የታወቁትን የባይዣን የቦታና ጌዜ ጂኦስታቲካዊ ሞዴሎችን በመጠቀም  እና አዳዲስ የጥገኛ ተዋሲያን ዳሰሳ ጥናቶች የመረጃ ቋት እንዲሁም በፀረ ወባ ትንኝ ኬሚካል የተነከረ አጎበር (አይቲኤን) ሽፋን እና የህክምና ውጤታማነትን በማካተት የወባ በሽታ ህመም እና ሞት በሚበዛባቸው የአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ ጂኦስፓቲካል ግምቶችን አመንጭተናል:: ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ ችግሮች በሌሉበት ሁኔታ በአፍሪካ ውስጥ ሊከሰት የሚችለውን የወባ ሸክም የመነሻ ግምት በማስቀመጥ ውጤታማ  የፀረ-ወባ መድኃኒት እና የአይቲኤን ስርጭት (በመደበኛ የመገኛ መንገዶች እና በጅምላ ዘመቻዎች) በተለያየ መጠን በመቀነስ ትንተናውን ለዘጠኝ መላምታዊ ሁኔታዎች ደጋግመን ሰራነው::

### ግኝቶች

ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ ምክንያት የወባ መከላከያ ሽፋን ካልተቋረጥ እ.ኤ.አ በ 2020 የወባ በሽታ በተስፋፋባቸው በሁሉም የአፍሪካ ሀገሮች 215·2 (95% እርግጠኛ ያልሆነ ክፍተት 143·7–311·6) ሚሊዮን ሰዎች በበሺታው እንደሚያዙ እና 386·4 (307·8–497·8) ሺህ እንደሚሞቱ በእኛ የመነሻ መላምት ገምተናል:: ውጤታማ የፀረ-ወባ መድሃኒት ሕክምና ተደራሽነት በከፍተኛ ሁኔታ ከቀነስ በወባ በሽታ የሚያዙ እና የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር እንደሚጨምር የእኛ ሞዴል አሳይቷል:- በዚህም የመከላከያ መድሃኒት ሽፋን በ25% ሲቀንስ 224·1 (148·7–326·8) ሚሊዮን ሰዎች ይታመማሉ እንዲሁም 487·9 (385·3-634·6) ሺህ ሰዎች ይሞታሉ ፤ የመከላከያ መድሃኒት ሽፋን በ50% ሲቀንስ 233·1 (153·7–342·5) ሚሊዮን ሰዎች ይታመማሉ እንዲሁም 597·4 (468·0–784·4) ሺህ ሰዎች ይሞታሉ ፤ የመከላከያ መድሃኒት ሽፋን 75% ሲቀንስ ደግሞ 242·3 (158·7–358·8) ሚሊዮን ሰዎች ይታመማሉ  እንዲሁም  715·2 (556·4–947·9) ሺህ ሰዎች ይሞታሉ:: የታቀደውን የ2020 አይቲኤን የጅምላ ማከፋፈያ ዘመቻዎችን ማቋረጥ እና መደበኛ የአይቲኤን ስርጭቶችን ከ25% - 75% መቀነስ  የወባን  ጫና ይጨምረዋል:- በ25% ሲቀንስ በድምሩ ወደ  230·5 (151·6–343·3) ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ይታመማሉ እንዲሁም 411·7 (322·8–545·5) ሺህ ሰዎች ይሞታሉ ፤ በ50% ሲቀንስ  232·8 (152·3–345·9) ሚሊዮን  ሰዎች ይታመማሉ እንዲሁም 415·5 (324·3–549·4)  ሺህ ሰዎች ይሞታሉ ፤ በ75% ሲቀንስ 234·0 (152·9–348·4) ሚሊዮን ሰዎች ይታመማሉ እንዲሁም 417·6 (325·5–553·1) ሺህ ሰዎች ይሞታሉ:: የአይቲኤን እና የፀረ-ወባ መድሃኒት ሽፋን በተመሳሳዩ ሁኔታ ሲቀንስ የወባ በሽታ ጫና በጅጉ ይጨምራል:- በ25% ሲቀንስ በወባ በሽታ 240·5 (156·5–358·2) ሚሊዮን  ሰዎች ይታመማሉ  እንዲሁም 520·9 (404·1–691·9) ሰዎች ይሞታሉ፤ በ50% ሲቀንስ 251·0 (162·2–377·0) ሚሊዮን  ሰዎች ይታመማሉ  እንዲሁም 640·2 (492·0–856·7) ሰዎች ይሞታሉ፤ በ75% ሲቀንስ በወባ በሽታ 261·6 (167·7–396·8) ሚሊዮን  ሰዎች ይታመማሉ  እንዲሁም 768·6 (586·1–1038·7) ሰዎች ይሞታሉ፤

### ትርጓሜ

ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ አሉታዊ ሁኔታዎች በወባ መቆጣጠር ላይ የሚፈጥሩት ችግሮች በአፍሪካ እ.ኤ.አ. በ 2020 በወባ በሽታ የሚሞቱ ሰዎችን ቁጥር በእጥፍ ሊጨምር ይችላል ፤ በሚቀጥሉት ዓመታት እንኳን የበለጠ ጭማሪን ያስከትላል፡፡ በወባ በሽታ ላይ የታየው የሁለት አስርት ዓመታት እድገት እንዳይቀለበስ እና ይህንን የህዝብ ጤና አደጋ ለማስወገድ ከኮቪድ-19 ምላሽ ጎን ለጎን ቅድሚያ ተሰቶት በቅንጀት የሚሰራ ተግባር ሁኖ መቀጠል አለበት::



### የገንዘብ ድጋፍ

ቢል እና ሜሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን ፤ ቻናል 7 ቴሌቶን ትረስት በምራብ አውስትራሊያ